# በየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የተዘጋጀ የ2011 ዓ.ም

# የ10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት “ናሙና” ፈተና

<u>***መመሪያ***</u>

1. ይህ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፈተና ነው፡፡ ፈተናውን ለመስራት የተፈቀደው 1፡30 ሰዓት ሲሆን ከ1፡30 ሰዓት በላይ መስራት አይፈቀድም፡፡
2. ፈተናውን ለመስራት ከተፈቀደው ሰዓት አስቀድመህ/ሽ ከጨረስክ/ሽ የሰራኸውን /ሽውን እንደገና መከለስ ትችላለህ/ሽ፡፡
3. እያንዳንዱን የጥያቄዎች መመሪያ በጥንቃቄ አንብብ/ቢ፡፡
4. ስለ ፈተናው ጥያቄ ካለህ/ሽ ፈተናው ከመጀመሩ በፊት ፈታኙን/ኟን መጠየቅ ትችላለህ/ሽ፡፡
5. እያንዳንዱ ጥያቄ አራት አማራጮች አሉት፡፡ ጥያቄዎቹንና አማራጮቹን በጥንቃቄ ካነበብክ/ሽ በኋላ መልስህን/ሽን በመልስ መስጫ ወረቀቱ ላይ በትክክል አጥቁር/ሪ፡፡

   ለምሳሌ መልስህ/ሽ ምርጫ 3 ከሆነ ከስሩ የሚገኘውን የአራት ማዕዘን ክፍት ቦታ በሚከተለው መልኩ በጥንቃቄ አጥቁር/ሪ፡፡




6. መልስህን/ሽን ለመቀየር ከፈለግህ/ሽ የመጀመሪያውን መልስ በደንብ አድርገህ/ሽ አጥፋ/ፊ በመቀጠል የተቀየረውን መልስ አጥቁር/ሪ፡፡
7. ከአንድ በላይ መልስ ማጥቆር ዋጋ ያሳጣል፡፡
8. ፈተናውን ለብቻህ/ሽ መስራት ይኖርብሃል/ሻል፡፡ በማንኛውም መንገድ ለማጭበርበር መሞከር ውጤቱን ያሰርዛል፡፡
9. ማጥቆር የሚቻለው በዕርሳስ ብቻ ነው፡፡

ፈተናውን እንድትጀምር/ሪ እስኪነገር ድረስ ይህንን ገጽ መግለጽ አይፈቀድ!!!

# PREPARD BY YEKA SUB CITY EDUCATION CENTER

# GRADE 10 AMHARIC MODEL EXAMINATIONS

GINBOT 2011 /MAY 2019

## GENERAL DIRECTIONS

THIS BOOKLET CONTAINS **AMHARIC** EXAMINATION. THE SUBJECT CODE FOR THIS EXAMINATION IS **01.** PLEASE COPY THESE CODES ON YOUR ANSWER SHEET WHERE IT READS BOOKLET CODE AND SUBJECT CODE. THEN, BLACKEN THE CORRESPONDING BOXES IN THE COLUMNS BELOW EACH NUMBER.

THE EXAMINATION CONTAINS **90** ITEMS. ATTEMPT ALL THE ITEMS. FOLLOW THE INSTRUCTIONS ON THE ANSWER SHEET AND THE EXAMINATION PAPER EXACTLY. USE ONLY **PENCIL** TO MARK YOUR ANSWERS.

THERE IS ONLY **ONE BEST** ANSWER FOR EACH ITEM. CHOOSE THE BEST ANSWER FROM THE SUGGESTED OPTIONS AND BLACKEN THE LETTER OF YOUR CHOICE ON THE ANSWER SHEET. YOYR ANSWER MARK SHOULD BE HEAVY AND DARK, COVERING THE ANSWER SPACE COMPLETELY. PLEASE ERASE ALL UNNECESSARY PENCIL MARKS COMPLETELY FROM YOUR ANSWER SHEET. THE OPTICAL MARK READER (0MR) REJECTS ALL ANSWER SHEETS WITH UNNECESSARY PENCIL MARKS.

YOU WILL BE ALLOWED TO WORK FOR **1:30 HOURS.** IF YOU FINISH BEFORE TIME IS CALLED, YOU MAY GO BACK AND REVIEW. WHEN TIME IS CALLED, YOU MUST IMMEDIATELY STOP WORKING, LAY YOUR PEMCIL DOWN, AND WAIT FOR FURTHER INSTRUCTIONS.

ANY FORM OF CHEATING OR AN ATTEMPT TO CHEAT IN THE EXAMINATION HALL WILL RESULT IN AN AUTOMATIC DISMISSAL FROM THE EXAMINATION HALL AND CANCELLATION OF YOUR SCORE(S)

**DO NOT TURN THIS PAGE UNTIL YOU ARE TOLD TO DO SO.**

## በየካ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የተዘጋጀ የ2011 ዓ.ም የ10ኛ ክፍል

## የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት "ናሙና" ፈተና

***መመሪያ ፩:- ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ፲፪ ጽህፈትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ / ምረጪ።***

1. አዜብ በጣም ቆንጆ ሴት ናት። ዐይኖቿ የንጋት ኮከብ ይመስስል ከርቀት ያበራሉ። የጥርሶቿ ንጣት ከሀጫ በረዶ ይስተካከላል። ፀጉሯ የሐር ነዶ ይመስል ትከሻዋ ላይ ተነስንሷል። አዜብ ሁሉን አሟልቶ የሰጣት ውብ ሴት ናት።

   (ከኃይለ ቃሉ መገኛ አንፃር የዚህ አንቀጽ ቅርጽ የትኛው ነው?)

   A.  B.  C.  D. 

2. በአንድ በተወሰነ ርዕስ ላይ የሀሳብ መለዋወጥ ተደርጎ ድምዳሜ ወይም የመፍትሔ ሃሳብ ላይ የሚደረስበት የቡድን ስራ ምን ይባላል?

   A. ክርክር B. ንግግር C. ጭውውት D. ውይይት

3. ከሚከተሉት አንዱ የተግባር ቅደም ተከተል ትስስር ያላቸውን ዓረፍተ ነገሮችን ለማያያዝ ያገለግላል።

   A. በጥቅሉ B. ከዚያም C. ወይም D. ስለሆነም

4. "ግለ ታሪክ" በሚጻፍበት ጊዜ መጠቀም ያለብን የትኛውን መደብ ነው?

   A. አንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር C. ሶስተኛ ቁጥር ነጠላ ቁጥር ተባዕት

   B. ሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ተባዕት D. ሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እንስት

5. የዘገባ ጽሁፍን ከሌሎች የጽሁፍ ዓይነቶች ልዩ **የሚያደርገው** ምንድነው?

   A. ልቦለዳዊ ጭብጥ ያለው መሆኑ C .የፈጠራ ውጤት በመሆኑ

   B. በውበት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ D. በእውነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ

6. አንድን ጽሁፍ አሳጥሮ ለመጻፍ ትክክለኛው ዘዴ የትኛው ነው?

   A. በጥልቀት ማንበብ C. ሀሳቡን ማብራራት

   B. ሀሳቡን መገልበጥ D . ሀሳቡን እንዳለ መፃፍ

7. ከሚከተሉት መካከል መልዕክትን የመቀበያ ክሂሎች የሚያሳየው የቱ ነው?

   A. ማዳመጥና መናገር C. ማዳመጥና መጻፍ

   B. ማዳመጥና ማንበብ D . ማዳመጥና መስማት

8. ቀጥሎ በአንድ ቃለ-ጉባኤ አፃፃፍ ውስጥ ሊቀርቡ የሚችሉ ነጥቦች ናቸው፡፡ ነገር ግን ቅደም ተከተላቸው ተዘበራርቋል ሲስተካከል የትኛውን ይመስላል?

1. በስብሰባ ላይ የተገኙ አባላት ስም ዝርዝር
2. የውይይትና የውሳኔ ሀሳብ
3. የመወያያ አጀንዳ
4. ስብሰባ የተካሄደበት ቀን፣ቦታ፣ሰዓት፣ የስብሰባ ዓይነት
5. የስብሰባው ርዕስ

A. 4,5,1,3,2 B. 5,4,1,2,3 C . 5,4,1,3,2 D . 4,5,3,2,1

9. የአንድ የስራ ደብዳቤ አካሄድ በተመለከተ ከሚከተሉት አንዱ ትክክል **አይደለም**፡፡

A. የስራ ደብዳቤ ከመስሪያ ቤት ወደ ግለሰብ ይላካል፡፡

B. የስራ ደብዳቤ ከአንድ ግለሰብ ወደ ሌላ ግለሰብ ይላካል፡፡

C. የስራ ደብዳቤ ከግለሰብ ወደ መስሪያ ቤት ይላካል፡፡

D. የስራ ደብዳቤ ከመስሪያ ቤት ወደ መስሪያ ቤት ይላካል፡፡

10. ትምህርቷን በሚገባ ተከታትላለች-----------በፈተናዋ ጥሩ ውጤት አስመዝግባለች፡፡ ሁለቱን ዓረፍተ ነገሮች ለማገናኘት ተመራጭ የሆነው አያያዥ ቃል የትኛው ነው?

A. ከዚያም B . ቢሆንም C . ስለዚህ D . ለነገሩ

11. ከሚከተሉት አንዱ የአንድ ዘገባ ባህርይ **አይደለም**፡፡

A. ወቅታዊነት B. ተጨባጭነት C . ትክክለኛነት D. ግምታዊነት

12. ከሚከተሉት አንዱ የአንቀጽ ኃይለ ቃል ተጨማሪ መጠሪያ **አይደለም**፡፡

A. ርዕሳዊ ዓረፍተ ነገር C . መንደርደሪያ ዓረፍተ ነገር

B. መሪ ዓረፍተ ነገር D . መቋጫ ዓረፍተ ነገር

***መመሪያ ፪፡- ከተራ ቁጥር ፲፫ እስከ ፲፮ ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ሥርዓተ ነጥብን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹን በጥሞና በማንበብ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡***

13. በጽህፈት ጊዜ የተረሳ ሆሄ ወይም ቃል ለማስገባት የምናመለክትበት ሥርዓተ ነጥብ ምን ይባላል?

A. ነጠብጣብ B . ሠረዝ C. ጭረት D. እመጫት

14. ህመሙ እያደር እየባሰበት መጥቷል----------- እስከ አሁን ለክሩ አልሰጠውም፡፡

( ከላይ በቀረቡት ሁለት ዓረፍተ ነገሮች መካከል ሊገባ የሚችለው ሥርዓተ ነጥብ ምንድነው?)

A. አራት ነጥብ B. ድርብ ሠረዝ C. ነጠላ ሠረዝ D . ሠረዝ

15. ነጋዴዋ ገበያ ሄዳ ብረት ድስት፣ ስኳር፣ ድንች፣ መርፌ፣ ቁልፍ እና ብረት ምጣድ ገዛች።

( በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የቀረቡት ተዘርዛሪ ነገሮች ስንት ናቸው?)

A . ስድስት B . አራት C . ሰባት D. ስምንት

16. ከሚከተሉት መካከል ትክክለኛውን የሥርዓተ ነጥብ አገባብ የያዘው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

A. "ሰላም የእድገት መሰረት ነው። ሲሉ" በርካታ ምሁራን ያትታሉ።

B. ሰላም የእድገት መሰረት ነው። "ሲሉ በርካታ ምሁራን ያትታሉ።"

C. "ሰላም የእድገት መሰረት ነው።" ሲሉ በርካታ ምሁራን ያትታሉ።

D . "ሰላም የእድገት መሰረት ነው። ሲሉ በርካታ ምሁራን ያትታሉ።"

17. ትክክለኛው የቅንፍ ሥርዓተ ነጥብ አገባብን የሚያሳየው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

A.ሴትየዋ (ቀዶ ጥገና) (ኦፕራሲዮን) ተደረገላት።

B. ሴትየዋ (ኦፕራሲዮን) ቀዶ ጥገና ተደረገላት።

C. ሴትየዋ ኦፕራሲዮን (ቀዶ ጥገና) ተደረገላት።

D. ሴትየዋ ቀዶ ጥገና (ኦፕራሲዮን) ተደረገላት።

**መመሪያ ፫:- ከተራ ቁጥር ፲፰ እስከ ፳፭ የቃላትና ሐረጋት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ**

18. ዓለሙ <u>ግንባራም</u> ነው። ( የተሰመረበት ፈሊጣዊ አባባል ትርጉም የሚሆነው የትኛው ነው?)

A. ግንባረ ትልቅ B. ደፋር C . ኮስታራ D. እድለኛ

19. "ጥፍር" (በዚህ ቃል ውስጥ ከሚገኙ ሆሄያት መካከል ጠብቆ የተነበበው የትኛው ነው?)

A . ፍ B . ጥ C. ር D. ጥ እና ፍ

20. ከሚከተሉት ጥንድ ቃላት መካከል ተቃራኒ ሆነው የተቀመጡት የትኞቹ ናቸው?

A. ዋጥ፣ስልቅጥ B. እጥር፣ ምጥን C. ብድግ ፣ቁጭ D. ጭንቅ፣ ጥብብ

21. “ጭምት” ብሎ “አመለኛ” ካለ “ሀሩር” ብሎ ---------------- ይላል፡፡

A. ቁር B. ወጀብ C. ቀጭ D. ብርድ

22. ሰውነትህ <u>የውሻ አፍንጫ</u> ሆኗል፡፡ ( የተሰመረበት ፈሊጣዊ አባባል ትርጉም የትኛው ነው?)

A. በጣም የሚያሸት B. በጣም የሚሞቅ C. በጣም የሚጠቁር ደ. በጣም የሚቀዘቅዝ

23. “ጥይት” ለሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺ የሚሆነው የትኛው ነው?

A. ነገረኛ B . ፈጣን C . ብልጥ D . ኃይለኛ

24. “ሕፀፅ” ብሎ እንከን ካለ ቢጋር ብሎ --------------- ይላል፡፡

A . ቅርጽ B. ፍንጭ C. ንድፍ D . ጅምር

25. ወዳ የመጣች ልጃገረድ <u>እግረ እርጥብ</u> ናት፡፡ (የተሰመረበት ፈሊጣዊ አባባል ትርጉም የቱ ነው?)

A. መልካም ዕድል የምታመጣ C . መልካም እድል የምታባርር

B. መልካም ዕድል የምታጨናግፍ D. መልካም ዕድል የምታሳጣ

**መመሪያ ፬፡- ከተራ ቁጥር ፳፮ እስከ ፶ ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ስዋሰውን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ፡፡**

26. ከሚከተሉት መካከል ስማዊ ሐረግ **የሆነው** የቱ ነው?

A . ቁምጣ ሱሪ B . ጨንቆኝ ነው C . በፍጥነት C. ወደ ቤት

27. ከሚከተሉት መካከል ገላጭ ሐረግ **የሆነው** የትኛው ነው?

A . በኪሱ B. ወደ ገበያ ሄደች C. ትልቅ ቋጥኝ D . ከጋራ ላይ

28.. በአዳራሹ ውስጥ <u>ሰዎች</u> ይወያያሉ፡፡ ( የተሰመረበት ቃል የቃል ክፍሉ ምንድነው?)

A . ቅጽል B . ስም C . ተውሳከ ግስ D . መስተዋድድ

29. ከሚከተሉት መካከል ልዩ **የሆነው** የትኛው ነው?

A. አዋቂ B . ሰነፍ C . ቀብር D . ትልቅ

30. ከሚከተሉት መካከል የእርባታ ምዕላድ የቱ ነው?

A. -ኢያ B . -ኣት C. -ነት D . -ኣማ

31. ሰውየው ብዙ ደክሞ የሰራው ቤት በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ። ( በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ግሳዊ ሐረጉ የትኛው ነው?)

A .የሰራው ቤት B. በአነስተኛ ዋጋ C.ሰውየው ብዙ ደክሞ D. በአነስተኛ ዋጋ ተሸጠ

32. "ኢትዮጵያዊ" (የዚህ ቃል መድረሻ ምዕላድ የትኛው ነው?)

A. -ዊ B. -ያዊ C. -ኣዊ D. -ጵያዊ

33. ከሚከተሉት መካከል አንድ ምዕላድ ብቻ ያለው ቃል የትኛው ነው?

A. ድርሰት B. ድመቷ C . ሆዳም D . ደብተሬ

34. ለአሉታዊ ዓረፍተ ነገር በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችለው የትኛው ነው።

A . መልሶችን በቀጥታ መንገድ ለመጻፍ ዝግጅት ያስፈልጋል።

B. መልሶችን በቀጥታ መንገድ መጻፍ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።

C . መልሶችን በቀጥታ መንገድ መጻፍ ይቻላል።

D . መልሶችን በቀጥታ መንገድ መጻፍ አይቻልም።

35. "አሰባሰበቻቸው" (በዚህ ቃል ውስጥ የሚገኘው ባለቤት አመልካች ቅጥያ የትኛው ነው?

A. -ኣቸው B. -ኧች C. -ቻቸው D. -ቸው

36. ተግታችሁ በመማር ብቁ ዜጋ ሁኑ። (ይህ ዓረፍተ ነገር በየትኛው መደብ የቀረበ ነው?)

A. በሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥር C. በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥር

B . በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር D. በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር

37. ከሚከተሉት ቃላት መካከል ቅጽል **ያልሆነው** የትኛው ነው?

A. ሀዘን B. ወልካፋ C. ወላድ D. ቁንጽል

38. ከሚከተሉት መካከል ለውስብስብ ዓረፍተ ነገር በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚችለው የትኛው ነው?

A. ተማሪው በሶስት የትምህርት ዓይነቶች ጥሩ ውጤት አስመዘገበ።

B. ከዲጃ በርካታ መጽሐፍት ገዛች።

C. ሰውየው ዕቃውን ከቦታው አጣው።

D. አስቴር ህመሟ የባሰባት ስላልታከመች ነው።

39. በግ የሚለው ስም ላይ ------- የሚለው ቅጥያ ሲጨመር የበጉ ጾታ ይታወቃል።

A. -ኤ B. -ኦች C. -ኡ D. -ኢቱ

40. የስም ገላጭ ቃላት ተግባር የስሙን -------------- ማገላት ነው።

A. ዓይነትን፣ መጠንን እና ግብርን

B. ጊዜን፣ መጠንን፣ እና ሁኔታን

C. ዓይነትን፣ መጠንን እና ቦታን

D. ሁኔታን፣ መጠንን እና ቦታን

41. የአንድ ቋንቋ መሠረቱ ምንድነው?

A. ቃል B. ድምጽ C . ሆሄ D. ዓረፍተ ነገር

42. "ካሰብንበት ለመድረስ በርትተን መስራት አለብን።"

(ዓረፍተ ነገሩ በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥር ቀርቧል። ይህ ዓረፍተ ነገር በሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር እንስት ጾታ ሲቀየር የትኛውን ይሆናል?

A. ካሰበበት ለመድረስ በርትቶ መስራት አለበት።

B. ካሰብኩበት ለመድረስ በርትቼ መስራት አለብኝ።

C. ካሰበችበት ለመድረስ በርትታ መስራት አለባት።

D. ካሰብሽበት ለመድረስ በርትተሽ መስራት አለብሽ።

43. ከሚከተሉት አንዱ የጥገኛ ምዕላዶች ባህርይ **አይደለም**።

A. ወደ ሌላ አነስተኛ ክፍል ሊሸነሸኑ ይችላሉ።

B. በራሳቸው ትርጉም የላቸውም።

C. ራሳቸውን ችለው አይቆሙም።

D. የመጨረሻ ንዑስ አሀድ ናቸው።

44. በሚቀጥለው ቀን ከእህቴ ጋር ክፍለ ሀገር እንሄዳለን፡፡

( በዚህ ዓረፍተ ነገር ውስጥ ያለው መስተዋድዳዊ ሐረግ የትኛው ነው?)

A. ከእህቴ ጋር B. በሚቀጥለው ቀን C. ክፍለ ሀገር D. ከእህቴ ጋር ክፍለ ሀገር

45. ከሚከተሉት መካከል ባለንብረትነትን የሚያመለክተው ቃል የትኛው ነው?

A. ገደላማ B. ቤትዋ C. አንዲት D. መንፈሳዊ

46. በምክንያትና ውጤት የተገነባው ዓረፍተ ነገር የትኛው ነው?

A. ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ የስርጭት ባህርይ አሁንም እምነት የሌላቸው ሰዎች አሉ፡፡

B. ሰላም የእድገት መሠረት መሆኑን የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር ገለጹ፡፡

C. በትምህርት ቤት ውስጥ በተነዛው አሉባልታ ምክንያት የተማሪዋ መንፈስ ታውኳል፡፡

D. ሁሉም ሰው በአመጋገብ የራሱን ጤንነት መጠበቅ እንዳለበት ገለጸ፡፡

47. ከሚከተሉት መካከል አንዱ የጥብቀት ትርጉም የለውም፡፡

A. ባቡር B. አባይ C.ጠብቆ D. ቀለብ

48. ከሚከተሉት መካከል በግዕዛዊ እርባታ ያልተመሰረተው ቃል የትኛው ነው?

A. መነኮሳት B. አብያት C. አናብርት D. ትዕግስት

49. ከሚከተሉት አንዱ ከግስ የተመሰረተ ቅጽል ነው፡፡

A. ወራሪ B. ወርሮ C. መውረር D. ወረራ

50. "አስጠረገቻቸው" ይህ ቃል ሲተነተን የትኛውን ይመስላል?

A. አስ-ጠረገ-ኧች-ኣቸው

B. አስ-ጠረገች-ኣቸው

C. አስ-ጠረገ-ቻቸው

D. አስ-ጠረገቻቸው

***መመሪያ ፩፡- ከተራ ቁጥር ፶፩ እስከ ፷ ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ***

ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ያሁኖቹ ጠበብት ጃፓናውያን አባቶች አንዲት መንደር ቆረቆሩና ስምዋንም "ዮዶ" ሲሉ ሰየሚት፡፡ ትርጉሙም ምስራቃዊ መግቢያ ማለት ነው፡፡ የነዋሪዎቹም ሙያ በአብዛኛው ዓሣን ማስገር ሆኖ የኑሮን ሀ…ሁ ተያያዙት፡፡

ታዲያ ይህንን መሰረት የጣሉባት ትንሽ መንደር ቀስ በቀስ እያደገችና በስልጣኔ እየገሰገሰች ሄደች። ይህንን የተመለከተው መራሄ መንግስት "ዮዶ" በወታደራዊ ስትራቴጂ ያላትን ጠቀሜታ፣ በግብርና የምታመርተውን የሩዝ ምርት፣ለዓሣ አጥማጆቹ ምቹ የሆነች ቦታ መሆኗን አይቶ በ1868 እ፣ኤ፣አ ለርዕሰ ከተማነት አጫት። ግንባታም ተጧጡፎ ዩኒቨርስቲዎች፣የጋዜጣ ማተሚያ ቤቶች፣ቲያትር ቤቶች፣ቤተ-መዘክሮች፣ የአራዊት ጥናትና ምርምር ተቋሞች፣ መናፈሻዎች፣ የኪነ ጥበባት ማዕከላት፣ የሳይንስ ማፍለቂያ ቤተ-ሙከራዎች ወዘተ ታነጹባት።

በተጨማሪም ከአብራኳ በፈለቁ ሊቃውንት የሚመሰረቱ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አውቶሞቢሎች፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥኖች፣የውሃ መምጠጫ ሞተሮች፣ካሜራዎች፣የህክምና መገልገያ ዕቃዎች፣ የታሸጉ ምግቦችን በማምረት ለዓለም ታበረክት ጀመር። ይህቺ 225 ስኴር ማይል ስፋት ያላት ከተማ ዓለም አቀፍ ግንኙነት የሚከናወንባት እምብርት ሆነች። የዓሣ ማምረቻ ፋብሪካዎችና ትልልቅ መርከቦቿ በስራ ተወጠሩ።

ይህቺ በመገስገስ ላይ ያለች እፁብ ድንቅ ከተማ በ1923 እ.ኤ.አ ያልተጠበቀ የመሬት መንቀጥቀጥ አደጋ ደረሰባትና ወደ ዶግ አመድነት ተቀየረች። ከነዋሪዎቿ መካከል 10,000 ሰዎችን በሞት አጣች። ይሁን እንጂ የተረፉት ነዋሪዎች ተስፋ ባለመቁረጥ "መከራን በመከራነቱ ሳይሆን በመካሪነቱ" በመቀበል የጃፓኗን ጥንታዊ ከተማ መልሰው መገንባት ተያያዙት። በጥቂት ጊዜያት በአዲስ መልክ በዘመናዊና በረቀቀ ጥበብ ኃይላቸውን አሰባስበው ከመጀመሪያው በበለጠ አነጿት። ከማዕበልና ከመሬት መንቀጥቀጥ ነፃ የሚያደርግ መሳሪያ ተጠቅመው በድጋሚ ገነቧት።

ዳሩ ምን ያደርጋል በ1940 እ.ኤ.አ የተቀሰቀሰው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት በትር ያችን የጃፓን ዓይን የሆነችውን "ዮዶ"ን አወደማት። 80% የሚሆነው የከተማይቱ አካል አመድ ሆነ። 90,000 ህዝብ ወደ አፈርነት ተቀየረ፣ 125,000 ህዝብ ለአካለ ስንኩልነት ተዳረገ። የጦርነት አሰቃቂነትን ለጃፓኖች መንገር "ለቀባሪው ማርዳት" ሆነ።

ነገር ግን አሁንም ጃፓኖች በጽኑ ሞራልና ብርታት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ለሶስተኛ ጊዜ "ዮዶ"ን አንፀው በአስር ዓመታት ውስጥ በድጋሚ ፈጠሯት። ስሟንም ቀይረው "ቶኪዮ" አሏት። በ1954 እ.ኤ.አ የዓለም የኦሎምፒክ ኮሚቴ ይህችን ውብ ከተማ ለስፖርታዊ የውድድር ቦታ አጯት። የማራቶን ጀግናው ኢትዮጵያዊው ሻምበል አበበ ቢቂላ ሁለተኛውን የወርቅ ሜዳሊያ አጠለቀባት። ሀገር እንዲህ ይገነባል!!!

ምንጭ፣ከዘነበ ወላ፣"ህይወት በባህር ውስጥ"፣1985 ዓ.ም

( ለፈተና እንዲሆን ተሻሽሎ የቀረበ።)

51. በሁለተኛው አንቀጽ ላይ መራሄ መንግስቱ የተመለከተውና የወሰነው ምንድነው?

A. የከተማዋን ስም “ዮዶ” ተብሎ እንዲጠራ

B. ከተማዋ በሁሉም ዘርፍ ምቹ በመሆኗ ለርዕሰ ከተማነት እንድትታጭ

C. ከተማዋ ለዓሣ አጥማጆቹ ምቹ መሆኗን

D. ከተማዋ ለወታደራዊ ስትራቴጂነት እንድታገለግል

52. ከሚከተሉት አንዱ **ስህተት** ነው፡፡

A. የጥንቶቹ ጠበብት ጃፓናውያን ላሁኖቹ መሰረት ጥለዋል

B.“ዮዶ” የጥንታዊ ጃፓን ርዕሰ ከተማ መጠሪያ ነው

C . ከአብራኳ በፈለቁ ሊቃውንት የተለያዩ ምርቶች ለዓለም አበረከተች

D. የዓለም የተለያዩ ሊቃውንት ከተማዋን እንድታድግ አሰተዋጽኦ ነበራቸው

53. አንቀጽ ሶስትንና አንቀጽ አራትን የገናኘው መሸጋገሪያ ቃል የትኛው ነው?

A. በተጨማሪም B. ይህቺ C. ይሁን እንጂ D. ዳሩ ምን ያደርጋል

54. ለምንባቡ ይበልጥ ተስማሚ ሊሆን የሚችለው ርዕስ የትኛው ነው?

A. ከዓሣ አጥማጆች መንደር ወደ ትልቅ የዓሣ አጥማጆች ከተማ

B. ከዓሣ አጥማጆች መንደር ወደ ዘመናዊቷ የውድድር ከተማ

C. ከዓሣ አጥማጆች መንደር ወደ ታላቅ ርዕሰ ከተማ

D. ከዓሣ አጥማጆች መንደር ወደ አበበ ቢቂላ የድል መንደር

55. የጽሁፉ ዋና መልዕክት ምንድነው?

A. ችግርን በጽናት በማለፍ ስኬት ላይ መድረስ እንደሚቻል

B. ችግር በተወሰኑ ሰዎች ላይ በጣም አስከፊ እንደሚሆን

C. ችግር በጽኑ ብርታት ቢታለፍም ሌላ የማይቻል ችግር እንደሚፈጠር

D. ችግር በጽናትና ብርታት ብቻ ሊታለፍ እንደሚቻል

56. በአንቀጽ አራት ላይ "መከራን በመከራነቱ ሳይሆን በመካሪነቱ መቀበል" ሲል ምን ማለቱ ነው?

A. ሰዎች ከችግር መማር እንደሚችሉ የተገለጸበት እሳቤ ነው

B. ሰዎችን የሚመክሩ አንዳንድ ችግሮች መኖራቸውን ለማሳየት ነው

C. ምክርና መከራ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው

D. ሰዎች መካሪነት ያላቸውን መከራዎች መምረጥ እንዳይሳናቸው የሚያሳይ ነው

57. የአንቀጽ አንድ ኃይለ ቃል በአንቀጹ ----------- ላይ ይገኛል፡፡

A. መካከል B. መጨረሻ C. መጀመሪያ D. መጀመሪያና መጨረሻ

58. በአንቀጽ አንድ ላይ…ሙያቸውም ዓሣን ማስገር ሆኖ… ይላል

( የተሰመረበት ሐረግ ተመሳሳይ ፍቺው የትኛው ነው?)

A. ዓሣን ማሳደድ B. ዓሣን ማነቅ C. ዓሣን ማጥመድ D. ዓሣን ማገት

59. አንቀጽ ሶስት ላይ …ኃይላቸውን አሰባስበው ከመጀመሪያው በበለጠ አነጿት፡፡…

( የተሰመረበት ቃል አገባባዊ ፍቺ የትኛው ነው?)

A. አፀዷት B. ገነቧት C. ቀረጿት D. ዳረጓት

60. በምንባቡ ውስጥ **እምብርት** የሚለው ቃል አገባባዊ ፍቺው ምንድነው?

A. የሰውነት አካል B. የሰዎች መገናኛ C. ማዕከላዊ ቦታ D. ርዕሰ ከተማ

**መመሪያ ፮:- ከተራ ቁጥር ፷፩ እስከ ፸ ድረስ ስነ-ጽሁፍን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጭ**

61. ከሚከተሉት መካከል ለተውኔትና ለልቦለድ የጋራ የሆነው ስነ-ጽሁፋዊ እሳቤ የትኛው ነው?

A. ትዕይንት B. ኮሜዲ C. ገቢር D . ታሪክ

62. ከሚከተሉት አንዱ የአንቀጽ ባህርይ **አይደለም**፡፡

A. በአንድ አንቀጽ ውስጥ አንድ ኃይለ ቃል ብቻ ይገኛል፡፡

B. በአንድ አንቀጽ ውስጥ ተያያዥነት ሀሳብ ያላቸው ዓረፍተ ነገሮች ይገኛሉ፡፡

C. በአንድ አንቀጽ ውስጥ ውስን ዝርዝር ዓረፍተ ነገሮች ይኖራሉ፡፡

D. በአንድ አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ ናቸው፡፡

63. ከሚከተሉት አንዱ የተውኔት ሙያዊ ቃል **አይደለም**፡፡

A. አዘጋጅ B. ገፀ ባህይ C. ፀሐፊ ተውኔት D. ተዋናይ

64. ጋብቻን ለመመስረት የቤተሰብ ጣልቃ ገብነት ያስፈልገዋል ወይስ አያስፈልገውም? ለሚለው ርዕስ ለየትኛው የድርሰት ዓይነት በመነሻነት ያገለግላል?

A. ለአመዛዛኝ ድርሰት B. ለተራኪ ድሰት C. ለስዕላዊ ድሰት D. ለገላጭ ድርሰት

65. ሾላ ገበያ በሰው ብዛት ተጨናንቋል፡፡ ሰው ከወዲያ ወዲህ ይላል፡፡ ዶሮ ስንት ነው?፣ እንቁላሉስ?፣ ሽንኩርት ስንት ገባ? ተመሳሳይ ጥያቄ ይጠየቃል፡፡ መልስ የሰጣል፡፡ አንዳንዱ ገዢ በተሰጠው የዋጋ መልስ ራሱን መያዝ ይዳዳዋል፡፡ ግና አማራጭ ባለመኖሩ ከድርድር በኋላ የተጠየቀውን ከፍሎ የፈለገውን ይወስዳል፡፡ የበዓል አውድ ለየት ይላል፡፡

( ከላይ የቀረበው አንቀጽ ለየትኛው የድርሰት ዓይነት መነሻ ይሆናል?)

A. ተራኪ ደርሰት B. ስዕላዊ ድርሰት C. ገላጭ ድርሰት D. አመዛዛኝ ድርሰት

66. “ሁሉም ለየብቻው እንደተለያየ፣

የኔም ሳቅ ለብቻው ከኔ ጋራ ቆየ፡፡”

(ይህንን ቃላዊ ግጥም የሚያንጎራጉረው ሰው --------------- ነው፡፡ )

A. ልዩ የሆነ ሰው B. ግራ የተጋባ ሰው C. ሳቂታ ሰው D. ብቸኛ ሰው

67. ከሚከተሉት አንዱ የአጭርና የረጅም ልቦለድ የጋራ ባህርይ **አይደለም**፡፡

A. የቅደም ተከተል ትረካ አካሄድ መጠቀማቸው C. በርካታ ገጸ ባህርያትን ማሳተፋቸው

B. የተለያየ ትረካ አቀራረብ መጠቀማቸው D. በግጭት የታጀቡ ትረካን ማቅረባቸው

68. በልቦለድ ውስጥ የታሪክ የምክንያትና ውጤት ትስስርን የሚያመለክተው አላባ ምን ይባላል?

A. ትልም B. ግጭት C. መቼት D. አንፃር

69. የገሐዱ ዓለም የህይወት ነፀብራቅ ሆኖ የሚቀረጽ የኪነ ጥበብ ዝርፍ ምን ይባላል?

A. ሥነ ግጥም B. ሥነ ተውኔት C. ሥነ ቃል D. ሥነ ጽሁፍ

70. ከሚከተሉት አንዱ የኢ- ልቦለድ ባህርይ **አይደለም**፡፡

A. ቀጥተኛ የመቼት ቅኝዎች አሉት

B. ለውበት እንጂ ለእውነት እምብዛም አይጨነቅም

C. ለደራሲው ሙሉ ነፃነት አይሰጥም

D. ከኪናዊ አቀራረብ ይልቅ ቀጥተኛ አቀራረቡ ያመዝናል

**መመሪያ ፯፡- ከተራ ቁጥር ፸፩ እስከ ፸፯ ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ግጥሙን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ**

**በረከተ መርገም ፪**

ምንም እንኳን ቲቪው ፥ ሳሎኔ ውስጥ ቢኖር፣
የቲቪው ኑሮ ግን ፥ ሳሎኔ ውስጥ የለም፡፡
  ኮምፒተር የሚሏት ፥ የደብተራ ሳጥን ፥ ከመጣች ጀምሮ፣
  በወግ መኖር ቀረ ፥ አስማት ሆነ ኑሮ፡፡
  ከተፈጥሮ ሽሽ ፥ ሰው ከሰው መነነ፣
  መኖርና መሞት ፥ ክሊክ ማድረግ ሆነ፡፡
ወንበር ላይ ተጥዶ ፥ ወንበር ላይ እንዲያረጅ፣
ትውልዱ ላይ አዚም ፥ የጣልክበት ፈረንጅ፡፡
የፌስቡክ ፈብራኪ ፥ ጎረምሳ ዲታ ሰው፣
የግፍ ንብትህን ፥ በልተህ ሳትጨርሰው፣
የየካው ሚካኤል ፥ ዓይንህን ያፍሰው!፡፡
  የሞባይል ፈጣሪ ፥ የቴሌፎን ጌታ፣
  በኖርክበት ዘመን ፥ ባለህበት ቦታ፣
  አቡነ አረጋዊ ፥ ይጣሉህ በቴስታ!፡፡

ምንጭ፡- በዕውቀቱ ሥዩም፣"የማለዳ ድባብ"፣2009 ዓ.ም ፥52፡፡

(ለፈተና እንዲስማማ ተደርጎ የተወሰደ፡፡)

71. "ኮምፒተር የሚሏት ፥ የደብተራ ሳጥን ፥ ከመጣች ጀምሮ፣

በወግ መኖር ቀረ ፥ አስማት ሆነ ኑሮ።"

( ይህ የግጥሙ ስንኝና ሐረጋት በየትኛው የዘይቤ ዓይነት የቀረበ ነው።)

A. በእንቶኔ ዘይቤ B. በምፀት ዘይቤ C. ተለዋጭ ዘይቤ D.አያዎ ዘይቤ

72. በግጥሙ ሊተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ምንድነው?

A. ትዝብት B. ቅናት C. ግርምት D. ንቀት

73. ከላይ የቀረበው ግጥም በየትኛው የግጥም ቤት ሊመደብ ይችላል?

A. ቤሄ በሉ ቤት B. የወል ቤት C. ሰንጎ መገን ቤት D . ፀጋዬ ቤት

74. የግጥሙ ጠቅላላ ቤት መድፊያ ቃላት የትኞቹ ናቸው?

A. የለም፣ ኑሮ፣ ሆነ፣ ያፍሰው፣ በቴስታ C. የለም፣ ኑሮ፣ ሆነ፣ ያፍሰው፣በቴስታ

B. ቢኖር፣ የለም፣ ኑሮ፣ ሆነ፣ ፈለንጅ ያፍሰው D. የለም፣ኑሮ፣ሆነ፣ፈረንጅ፣ያፍሰው፣በቴስታ

75. ግጥሙ በስንት አንጓ ወይም አርኬ ተከፋፍሎ የቀረበ ነው?

A. በሶስት B. በሁለት C. በአራት D. በአምስት

76. ግጥሙ በ-----------ስንኝና በ---------- ሐረግ የተገነባ ነው?

A. በ14፣28 B. 14፣29 C. 28፣14 D. 29፣14

**መመሪያ ፳:- ከተራ ቁጥር ፸፯ እስከ ፺ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ**

77. "መልካም ስም ከመቃብር በላይ ይውላል።" (የዚህ ምሳሌያዊ አባባል ትርጉም የቱ ነው?)

A. የሟች ስም መቃብር ላይ ይውላል C. ስም ለመጠሪያነት ያገለግላል

B. ስም ያለው ሞኝ ነው D. መልካም የሰራ ቢሞትም በስሙ ይታወሳል

78. "ቡሀቃቸውን ሳይከደኑ፣እኔን ሌባ ይላሉ።" አለ ውሻ።

( ይህ ምሳሌያዊ አባባል በየትኛው ዘይቤ የተገለጸ ነው?)

A. ሰውኛ ዘይቤ B. ተለዋጭ አይቤ C. ምፀት ዘይቤ D. እንቶኔ ዘይቤ

79. ከሚከተሉት መካከል የመናገር ክሂልን ይበልጥ የሚያዳብረው የትኛው ነው?

A. ንግግርን ማዳመጥና መጻፍ C. ንግግርን መጻፍና ማንበብ

B. ንግግርን አዳምጦ መናገር D. ንግግርን ማዳመጥና ማንበብ

80. ከሚከተሉት በካከል የክርክር አቀራረብ መመሪያ **ያልሆነው** የቱ ነው?

A. ፍሬ ሃሳቦችን በቅደም ተከተል ማቅረብ C. የመከራከሪያ ርዕሱን ማስተዋወቅ

B. ርዕሱን የተመለከተ ሃሳብ ማሰባሰብ D. የተሰጠውን የጊዜ ገደብ ማክበር

81. ከሚከተሉት መካከል ገንቢ ሃሳብ የያዘው ምሳሌያዊ አባባል የትኛው ነው?

A. ከሹም አይጣሉም ከግንብ አይታገሉም C. ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠንቀቅ

B. ሴት በማጀት ወንድ በችሎት D. ንጉስ መንቀፍ ነብር ማቀፍ

82. ከሚከተሉት መካከል አንብቦ መረዳትን ለመፈተሽ ሲታሰብ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ የቱ ነው?

A. ጽሁፉን በማንበቤ የተማርኩት ምንድነው?

B. የማላውቃቸውን ቃላት እንዴት መረዳት እችለላለሁ?

C. ጽሁፉን እንዴት አድርጌ ላንብበው?

D. የትኛውን የንባብ አይነት ልጠቀም?

83. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች መካከል የጥያቄ ምልክት የሚወስደው የትኛው ዓረፍተ ነገር ነው?

A. ጓኛዬን እንዴት ይቅርታ እንደምጠይቀው አላውቅም

B. ጓደኛዬ እንደተቀየመኝ አውቃለሁ

C. ጓደኛዬ ማን እንደሆንኩ አልተረዳኝም

D. ጓደኛዬን እንዴት ይቅርታ ልጠይቀው

84. የቋንቋን ስዋሰዋዊ ህግ ሳይጠብቅ በስንኞች ተሰናስሎ የሚቀርብ የጽሁፍ ቅርጽ ምን ይባላል?

A. ዝርው ጽሁፍ B. ግጥም ጽሁፍ C. ስድ ጽሁፍ D. ስነ ጽሁፍ

85. "አትረፍ ያለው በሬ --------------------------::"

( ይህንን ምሳሌያዊ አባባል ሊያሟላ የሚችለው የትኛው ነው?)

A. ሲያርስ ይሞታል C. ቆዳው ከበሮ ይሆናል

B. ታርዶ ስጋው ይበላል D. ቆዳው ገበያ ይሸጣል

86. ሁሉም ቋንቋዎች የተናጋሪያቸውን ወግ፣ ልማድ ወይም ባህል በተሟላ አኳኋን ይገልጻሉ ሲባል ምን ማለቱ ነው?

A. ቋንቋ ሰብዓዊ ነው C. ቋንቋ ምሉዕ ነው

B. ቋንቋ ዘፈቀዳዊ ነው D. ቋንቋ ረቂቅ ነው

87. ከሚከተሉት የሥነ ቃል ዘርፎች መካከል በግጥም የማይቀርበው የቱ ነው?

A. አፈ-ታሪክ B. ሙሾ C. ፉከራ D. ቀረርቶ

88. "እንካ ብላ አለችኝ ደረቁን እንጀራ፣

እሷ በነካካው በራሰው ልትበላ::" ( የዚህ ቅኔ ግጥም ህብረ ቃል የትኛው ነው?)

A. እሷ B. እሷ በነካካው C. በነካካው D. በራሰው

89. "የለመንኩሽ ብዕር ስለጠፋብሽ፣

እሰይ ደስ ብሎኛል ባልተገኘልሽ::" ( የዚህ ቅኔ ግጥም ሰም ፍቺ የትኛው ነው?)

A. እሰይ ደስ ብሎኛል C. ብዕርሽ ጠፍቶ በቀረብሽ

B. የትዳር አጋርሽ ብዕርሽን ወስዶታል D. የምታገቢው ባል ተገኝቶልሻል

90. "ጎመን ቀንጥስ አሉኝ ምንጊዜ ሊበስል፣

ይህንን ቀን ጥሼ እዘልቀው ይመስል::" ( የዚህ ቅኔ ግጥም ወርቅ ፍቺ የትኛው ነው?)

A. ይህንን ሁሉ ጎመን ቀንጥሼ አልዘልቀውም

B. ይህንን ሁሉ ጎመን ለመቀንጠስ አይመቸኝም

C. ይህ የመከራ ቀን ለጎመን መቀንጠስ አይሆንም

D. ይህንን የመከራ ቀን እሻገረዋለሁ ወይ

# መልስ

<u>መመሪያ ፩:-ጽህፈት</u>

1. ሐ
2. መ
3. ለ
4. ሀ
5. መ
6. ሀ
7. ለ
8. ሐ
9. ለ
10. ሐ
11. መ
12. መ

<u>መመሪያ ፪:-ሥርዓተ ነጥብ</u>

13. መ
14. ለ
15. ሀ
16. ሐ
17. መ

<u>መመሪያ ፫:-ቃላትና ሐረጋት</u>

18. መ
19. ሀ
20. ሐ
21. ሀ
22. መ
23. ለ
24. ሐ
25. ሀ

<u>መመሪያ ፬:-ስዋሰው</u>

26. ሀ
27. መ
28. ለ
29. ሐ
30. ለ
31. መ
32. ሐ
33. ሀ
34. መ
35. ለ
36. ሐ
37. ሀ
38. መ
39. ሐ
40. ሀ
41. ለ
42. መ
43. መ
44. ሀ
45. ለ
46. ሐ
47. ሀ
48. መ
49. ሀ
50. ሀ

<u>መመሪያ ፭:- ምንባብ</u>

51. ለ
52. መ
53. ለ
54. ሐ
55. ሀ
56. ሀ
57. ሐ
58. ሐ
59. ለ
60. ሐ

<u>መመሪያ፮:-ሥነ ጽሁፍ</u>

61. መ
62. ሐ
63. ለ
64. ሀ
65. ለ
66. መ
67. ሐ
68. ሀ
69. መ
70. ለ

<u>መመሪያ፯:-ሥነ ግጥም</u>

71. ሐ
72. ሀ
73. ለ
74. መ
75. ሐ
76. ለ

<u>መመሪያ ፰:- ልዩ ልዩ</u>

77. መ
78. ሀ
79. ለ
80. ለ
81. ሐ
82. ሀ
83. መ
84. ለ
85. ሐ
86. ሐ
87. ሀ
88. መ
89. ሐ
90. መ